ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ
Forum for Social Studies (FSS)

ሐምሌ 2002 ዓ.ም. የፖሊሲ ፍሬ ሀሳቦች ቁጥር 23

# የከተማ የምግብ ዋስትና፤ በአዲስ አበባ ልደታ ክፍለ ከተማ ላይ ያተኮረ ጥናት

የማኅበራዊ ጥናት መድረክ በሀገሪቱ የልማት ችግሮች ዙሪያ ፖሊሲ-ነክ ምርምሮችን የሚያደርግ ለትርፍ ያልተቋቋመና መንግስታዊ ያልሆነ አገር በቀል ድርጅት ነው።

የምርምር ውጤቶቹን ለፖሊሲ አውጪዎችና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርሱ ያደርጋል፤ ሕዝባዊ ውይይቶችን ያዘጋጃል፤ የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ጋብዞ ያወያያል።

በአዲስ አበባ (በ97.1 ሞገድ) እና በአዋሳ (በ100.9 ሞገድ) ከተሞች ኤፍ.ኤም.ራዲዮ ጣቢያዎች ልማት ነክ ጉዳዮችን እያዘጋጀ ያሰራጫል።

በድረ-ገጹ የሕትመት ውጤቶቹን ዝርዝር ያቀርባል።

በርዕሱ ዙሪያ ሐሳብ መስንዘር የምትፈልጉ በኢሜይል አድራሻችን ላኩልን።

## መግቢያ

ባለፉት ጥቂት ዓመታት በሌሎች አገራት እንደታየው ሁሉ በኢትዮጵያም የምግብ ዋጋ በከፍተኛ ደረጃ አሻቅቦ እንደነበር ይታወቃል። የዚህ የምግብ ዋጋ ንረት መነሾዎች ከአጠቃላይ የዋጋ ግሽበት፤ ከምግብ ፍላጎት እድገት ጋር ሲነጻጸር ዝቅተኛ የምግብ አቅርቦት እድገት፣ በውጭ ምንዛሬ ዕጥረት ምክንያት ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባ ምግብ ላይ ከተደረገው ገደብ ጋር እንደተያያዙ ይገመታል። ይህ የምግብ ዋጋ ንረት የተወሰነውን የምግብ አምራች ክፍል ቢጠቅምም በምግብ-አጠር የገጠር አካባቢዎችና ዝቅተኛ ገቢ ባላቸው የከተማ ነዋሪዎች ዘንድ አስከፊ የሆነ የምግብ እጥረት አስከትሏል። በ1997 ዓ.ም. የተካሄደው የቤተሰቦች ገቢ ፍጆታና ወጪ ጥናት እንዳሳየው በአዲስ አበባ ነዋሪ ከሆነው ሕዝብ ውስጥ ሰላሳ ሁለት በመቶ የሚሆነው ከአንጻራዊ ድህነትና የምግብ ድህነት ወለል በታች ነበር። ጥናቱ ከተካሄደበት ዓመት ወዲህ የተከሰተ የምግብ ዋጋ ንረት ይህንን አኃዝ ከፍ ሳያደርገው እንደማይቀር መገመት ይቻላል።

ይህ ጥናት በአዲስ አበባ ከተማ በድህነት ኑሮ ውስጥ የሚገኙ ቤተሰቦች መካከል የተከሰተውን የምግብ እጥረት ሁኔታና ያደረሰውን ተጽዕኖ መነሾዎቹንና ይህን የምግብ እጥረት ለመቋቋም የሚጠቀሙባቸውን ስልቶች ይዳስሳል። ጥናቱ ይህን የሚያከናውነው በልደታ ክፍለ ከተማ ላይ በማተኮርና ገላጭ (qualitative) የጥናት ስልቶችን በመጠቀም ነው።

## የጥናቱ ስፍራና ስልቶች

ጥናቱ የተካሄደው በአዲስ አበባ ውስጥ በድህነት ከሚታወቁት አካባቢዎች አንዱ በሆነው በልደታ ክ/ከተማ ነው። አንድ በ2000 ዓ.ም የተደረገ ጥናት እንደጠቆመው በልደታ ክ/ከተማ ከሚገኘው ሕዝብ ሃምሳ ሶስት ከመቶው ከአንጻራዊ የድህነት ወለል በታች ይገኝ ነበር። ከልደታ ክፍለ ከተማ ውስጥ ሶስት ቀበሌዎች ማለትም ቀበሌ 05/08፣ ቀበሌ 09/10 እና ቀበሌ 07/14 በጥናቱ ውስጥ ተካተዋል።

ጥናቱ ከምግብ ዋስትና ጋር የተያያዙ አመለካከቶችንና ሰብዓዊ ገጽታዎችን በተሻለ ሁኔታ ሊያንጸባርቅ የሚችለውን ገላጭ (አኃዛዊ ያልሆነ) ስልት ተጠቅሟል። ጥናቱ የተጠቀመባቸው የገላጭ ስልት ዓይነቶች የቡድን ውይይቶችና ጥልቅ የሆኑ ቃለ መጠይቆች ነበሩ። በዚህ መሰረት ከቤተሰብ አባወራዎችና እማወራዎች ጋር በቀበሌ 05/08 እና በቀበሌ 09/10 አንዳንድ የቡድን ውይይት ሲካሄድ በእያንዳንዱ የጥናት ቀበሌ ከ10 አባወራዎችና እማወራዎች ጋር ባጠቃላይ ሰላሳ ጥልቅ የሆኑ ቃለ መጠይቆች ተከናውነዋል። ከጥናቱ ተሳታፊዎች አብዛኞቹ በድህነት ኑሮ ውስጥ የሚኖሩና የወር ገቢያቸው ከሁለት መቶ እስከ ዘጠኝ መቶ ብር ብቻ የሚሆን ነበር። በምግብ ዋጋ ንረት፣ በዝቅተኛ ገቢያቸውና በሌሎች ምክንያቶች ሳቢያ የጥናቱ ተሳታፊዎች ከተለያዩ ጾታዎች የእድሜ ክልሎችና የስራ ዘርፎች የተውጣጡ ሲሆን በአነስተኛ ንግድ የሚተዳደሩ የቀን ሰራተኞች፣ መጠነኛ የሙያ ብቃት ያላቸው የግልና የመንግስት ሠራተኞች፣ ጡረተኞች፣ ስራ የሌላቸውና ለማኞች ተካተዋል። የጥናቱ ተሳታፊዎች ነሲባዊ በሆነ መንገድ ስላልተመረጡ ጥናቱ አይነተኛ በሆነ ረገድ እንጂ ስታትስቲካል በሆነ መልኩ የክ/ከተማውን ወይም የአዲስ አበባን ሁኔታ ማንጸባረቅ ይችላል ማለት አይቻልም።

## የጥናቱ ግኝቶች

### የምግብ ዓይነቶችና የአመጋገብ መጠን

በድህነት ኑሮ ውስጥ የሚገኙት የጥናቱ ተሳታፊዎች የሚመገቧቸው የምግብ ዓይነቶች የሚከተሉት ናቸው፦ ከጤፍ፣ ከስንዴ፣ ከበቆሎ ወይም ከማሽላ ከሚሰራ እንጀራ ጋር የሚበሉ እንደ ሽሮ፣ የምስር ወይም የአተር ክክ ወጥና የተለያዩ አታክልት ሲሆኑ እነዚህ ከሌሉ በጨው፣ በበርበሬ፣ በሚጥሚጣ፣ ወይም ከቲማቲምና በርበሬ በሚሰራ ስልስ ሊተኩ ይችላሉ። ሌሎች ምግቦችም ብቻውን ወይም ከበርበሬና ከሚጥሚጣ ጋር የሚበላ ዳቦ፣ ቂጣ፣ ሽሮ ወይም በሶ የሚሰራበት የፋፋ ምግብ፣ ቆሎ፣ ቅንጬ እና ቆሎ ሲሆኑ በአሁኑ ወቅት አልፎ አልፎ ብቻ ለምግብነት የሚውሉት ስጋ፣ ፓስታ፣ መኮሮኒና ሩዝ ናቸው።

በጥናቱ የተካተቱት የልደታ ክፍለ ከተማ ነዋሪዎች አመጋገባቸው ከ1998 ዓ.ም ወይም ከ1999 ዓ.ም ጀምሮ እንደቀነሰ ይናገራሉ። የምግብ ዋጋ ንረትና ተያያዥ የሆነው

የምግብ እጥረት በከፍተኛ ደረጃ የጨመረው ግን ከ2000 ዓ.ም አጋማሽ ጀምሮ እንደነበር ያመላክታሉ፡፡ ስለዚህም ጥናቱ እንደሚያሳየው በአነስተኛ የኑሮ ደረጃ የሚገኙት የልደታ ክፍለ ከተማ ነዋሪዎች የምግብ ግዢና የአመጋገብ መጠን በጣም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንደደረሰ ያሳያል፡፡ ብዙ ቤተሰቦች የምግብ ግዢያቸውን እንዲቀንሱ በመገደዳቸው በአማካይ አንድ ቤተሰብ በወር ከአስር እስከ ሃያ አምስት ኪሎ ግራም እህልና አምስት ኪሎ ሽሮ ብቻ መሸመት የሚችልበት ሁኔታ ሲታይ ይህ እንኳ ከአቅማቸው በላይ ሆኖ በየእለቱ እንጀራና ዳቦ ለመግዛት የሚገደዱ ጥቂት አይደሉም፡፡ በዚህ ዝቅተኛ የምግብ ግዢ መጠን ሳቢያ ብዙ ቤተሰቦች ለቁርስ በነፍስ ወከፍ አንድ ዳቦ ወይም አምባሻ ብቻ ከሻይ ወይም ከውሃ ጋር መመገብ ሲችሉ ሌሎች ቤተሰቦች ደግሞ በጥቅሉ አንድ ወይም ሁለት ቁራጭ እንጀራ ከሽሮ ጋር ይመገባሉ፡፡ ይሁን እንጂ በጥናቱ ውስጥ ከተካተቱት ቤተሰቦች መካከል ግማሾቹ ውስጥ ወጣቶችና ጎልማሶች በወትሮው ቁርስ ሳይመገቡ ሲቀሩ ቁርስ ሳያገኙ ወደ ት/ቤት የሚሄዱ ልጆችም አሉ፡፡

ለምሳ ደግሞ በአብዛኛው አንድ ግለሰብ ግማሽ ወይም ሩብ እንጀራ ብቻ የሚመገብበት ሁኔታ ሲታይ ከዚህም ጋር የሚበላው ሽሮ የተለያየ ይዘት ያለው ሲሆን ሽንኩርትና ዘይት ሳይኖረው የሽሮ ዱቄትና ውሃ ብቻ ያካተተ ሊሆንም ይችላል፡፡ አንዳንድ ቤተሰቦች ምሳቸው ቆሎና ቡና ወይም ውሃ ብቻ ሲሆን ሌሎች ከነአካቴው ምንም ሳይመገቡ ይውላሉ፡፡ የዕለቱ የዕራት ሁኔታ ከምሳ ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡ ብዙዎቹ ቤተሰቦች አመጋገባቸውን በቀን ሁለት ጊዜ ብቻ አልፎ አልፎም በቀን አንድ ጊዜ ለመገደብ ተገደው ነበር፡፡ ይህ ዓይነቱ አመጋገብ ቤተሰቡን ከዕለት ወደ ዕለት ሕይወታቸውን ለማቆየት የሚያስችል ብቻ ስለሆነ አብዛኞቹ የጥናቱ ተሳታፊዎች አመጋገባቸውን በሚመለከት የሚሰማቸውን ብስጭት ይገልጹ ነበር፡፡

ጥናቱ በተካሄደበት ማህበረሰብ እንደ ሌሎች የከተማ ነዋሪዎች በቀን ሶስት ጊዜ የመመገብ ልማድ ቢኖርም ብዙዎቹ ቤተሰቦች አመጋገባቸውን በቀን ሁለት ጊዜ ብቻ ለመገደብ ተገደው ነበር፡፡ ከፍተኛ ቁጥር ባላቸው ቤተሰቦች ዘንድ ቁርስ ለልጆች ብቻ እንጂ ለአዋቂዎች አይቀርብም፡፡ በአንጻሩ አንዳንድ ቤተሰቦች ረፈድ አድርጎ ቁርስ በማድረግና እራታቸውን ቀደም አድርገው በመብላት ምሳቸውን ይታዉታል፡፡ በአንዳንድ ቤተሰቦች መካከል አዋቂዎች አልፎ አልፎም ልጆች በቀን አንድ ጊዜ ብቻ የሚመገቡበት አጋጣሚ አለ፡፡

በጥናቱ ተሳታፊዎች ዘንድ ለልጆች ከሚደረገው ልዩ እንክብካቤ ውጭ በቤተሰብ አባላት መካከል የአመጋገብ ልዩነት የማድረግ ልማድ ጎልቶ አልታየም፡፡ ከፍተኛ የምግብ እጥረት ሲከሰት ግን ልጆችም አመጋገባቸውን መቀነስ ይኖርባቸው ይሆናል፡፡ ሴቶች ግን ለሌሎች የቤተሰብ አባላት ቅድሚያ በመስጠት አመጋገባቸውን ሲገድቡ ይታያል፡፡

## የምግብ ዕጥረት መንስኤዎች

በጥናቱ በተዳሰሰው ማህበረሰብ ውስጥ ለሚታየው የምግብ እጥረት እንደ ዋና መንስኤ ሆኖ የተጠቀሰው የምግብና የሌሎች መሰረታዊ ቁሳቁሶች የዋጋ ንረት ነው፡፡ የዋጋ ንረቱና ተያያዥ የሆነው  የምግብ እጥረት በተለይ በ1998 ዓ.ም እና በ1999 ዓ.ም እንደጀመረ ሲነገር በተለይ በ2000 ዓ.ም አጋማሽ ፈጣንና ከፍተኛ በሆነ ሁኔታ መጨመሩ ሪፖርት ተደርጓል፡፡ የተለያዩ የጥናቱ ተሳታፊዎች የምግብ ዋጋ ንረቱ መንስኤዎች የነጻ ገበያው ሥርዓት፣ በገበሬዎችና በነጋዴዎች ዘንድ ይኖራል ተብሎ የሚታሰበው እህልን ከገበያው የማቀብ ዝንባሌ፣ ሕገወጥ የእህል ኤክስፖርትና የሕዝብ ብዛት እድገት ሊሆኑ እንደሚችሉ ይገምታሉ፡፡

ከዋጋ ንረት በተጨማሪ ለምግብ እጥረት መከሰት ሌሎች ምክንያቶች ተጠቃሽ ሆነዋል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ በተለያየ ምክንያት የሚከሰት የስራ ወይም የገቢ ምንጭ መቋረጥ፣ ነባራዊ የድህነትና የስራ እጦት፣ ነዋሪዎች በሽያጭ ለሚያቀርቧቸው ቁሳቁሶችና አገልግሎቶች የገበያ ፍላጎት መዳከምና ለቤተሰብ አባላት ሙያዊ ትምህርትና ስልጠና የሚወጣ ወጪ ይገኙበታል፡፡ እነዚህን የመሳሰሉና ሌሎች መነሾዎች ተደራርበው የአንድን ቤተሰብ የምግብ እጥረት የሚያባብሱበትም ጊዜ አለ፡፡

## የምግብ እጥረት ተፅዕኖ

ጥናቱ በተከናወነበት ማህበረሰብ የተንሰራፋው የምግብ ዕጥረት በብዙ ቤተሰቦች ላይ የተለያዩ አሉታዊ ሁኔታዎችን አስከትሏል፡፡ ከእነዚህ አንዱና ዋነኛው በአዋቂዎችና በልጆች ዘንድ የሚከሰት ቀጣይ የሆነ የረሃብ ስሜት ነው፡፡ ልጆች ረሃብ ሲሰማቸው የመነጫነጭ ባሕርይ ሲታይባቸው አዋቂዎችም በቀን አንዴ ብቻ መመገብ የሚገደዱበትን ጊዜ በትዕግስት ማሳለፍ ሲያስቸግራቸው ይታያል፡፡ ጥቂት ቤተሰቦች ደግሞ በተደጋጋሚ የሚሰማቸውን የረሃብ ስሜት የመላመድ አዝማምያ ይታይባቸዋል፡፡ ሌሎች ግን የሰውነት ድካም እንደሚሰማቸው ሲገልጹ ቀጣይ የሆነ የጭንቀትና ተስፋ የመቁረጥ ስሜት የሚያጠቃቸውም ጥቂት አልነበሩም፡፡

በሰውነታቸውና በጤናቸው የደረሰ ለውጥን በሚመለከት አንዳንዶች ምንም ዓይነት ለውጥ እንዳላስተዋሉ ቢገልጹም በዛ ያለ ቁጥር ያላቸው የጥናቱ ተሳታፊዎች ግን በእነሱና በቤተሰባቸው አባላት ላይ የሰውነት ክብደት መቀነስ እንደሚታይ ተናግረዋል፡፡ እንዲሁም አነስተኛ የማይባሉ ተሳታፊዎች ከምግብ እጥረት የተነሳ ቤተሰባቸው ውስጥ እንደ ጉንፋን፣ ሳል፣ የጉሮሮ ሕመም፣ የራስ ማዞር፣ የደም ማነስ፣ የጨጓራ ሕመም፣ ብርድና ምች የመሳሰሉት አንዳንድ ሕመሞች እንደተከሰቱ ገልጸዋል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ የምግብ እጥረት በልጆች የመማርና በአዋቂዎች በስራ የመሳተፍ እድልና ብቃት ላይ የተለያየ ተጽእኖ አሳርፏል፡፡ አንዳንድ ልጆች በረሃብ ምክንያት ወደ ት/ቤት መሄድ ሳይችሉ ሲቀሩ ሌሎች ደግሞ የቤተሰባቸውን የምግብ ፍላጎት ለማሟላት ሲሉ በስራ ዓለም ስለሚሰማሩ ለመማር ሳይችሉ ቀርተዋል፡፡ በቂ ምግብ ያልተመገቡ ተማሪዎች በክፍላቸው የሚሰጣቸውን ትምህርት በአግባቡ ለመከታተልና ጥናታቸውን ለማከናወን ሳይችሉ ይቀራሉ፡፡ የተወሰኑ ጉልበት በሚጠይቁ ስራዎች ላይ የተሰማሩ ወላጆችም ስራቸውን በብቃት ማከናወን እንዳልቻሉ ገልጸዋል፡፡

## የምግብ እጥረትን የመቀቋቋሚያ ዘዴዎች

የከተማ ነዋሪዎች የምግብ እጥረትን ለመቋቋም ወይም ለማሳለፍ የሚጠቀሙባቸው የተለያዩ ዘዴዎች አሉዋቸው፡፡ ከእነዚህ ዘዴዎች አንዱ ከገበያ የሚገዟቸውን የምግብ መጠንና ዓይነቶች በከፍተኛ ደረጃ መቀነስ ነው፡፡ ለምሳሌ በቀድሞው ሲገዙ በነበሩት ጤፍ ምትክ ዋጋቸው የሚቀንስ ሌሎች እህሎች፣ በመንግስት በተደጎመ ዋጋ የሚሸጥ ስንዴና ተጋግሮ የሚሸጥ እንጀራ ይሸምታሉ፡፡ ከእህል ሌላ እንደ ሽሮ፣ ምስር፣ ሽምብራ ክክ አትክልት፣ በርበሬና ዘይት የመሳሰሉ የምግብ ዓይነቶችን ግዢ ሲቀንሱ፣ በተለይ እንደ ፓስታ፣ ሥጋ ፣ፍራፍሬ፣ እንቁላልና ወተት ዓይነቶቹን

ደግሞ ጨርሶ ይተውታል።

ሌላው ተያያዥ ዘዴ የቤተሰቡን አመጋገብ በመጠንም ሆነ በዓይነት መቀነስ ነው። ይህ ዘዴ ቤተሰቦች የሚመገቡትን እንጀራ መቀነስ ወይም በዳቦ መተካት፣ እንጀራ ለመጋገር በጤፍ ፋንታ ሌሎች እህሎች መጠቀም፣ በሌላ ምግብ ፋንታ ቆሎ ወይም ንፍሮ ብቻ መመገብ፣ ከጓያ የሚሰራ ወይም ዘይት ሽንኩርትና በርበሬ የሌለው ሽሮ መመገብ፣ ሲብስ ደግሞ በሽሮ ፋንታ እንደ ቃሪያ በርበሬ ሚጥሚጣ ጨውና ስልስ የመሳሰሉትን በማባያነት መጠቀምን ያካትታል። በተጨማሪም ብዙዎች በቀን ሁለት ጊዜ ብቻ ሲመገቡ አንዳንዶች በቀን አንዴ በመመገብ የገጠማቸውን የምግብ እጥረት ለማሳለፍ ይጥራሉ። ተጨማሪ የምግብ አዘገጃጀትና አመጋገብ ስልቶች ደግሞ ነዳጅና የምግብ ቁሳቁሶችን ለመቆጠብ በቀን አንድ ጊዜ ብቻ መቀቀል፣ በእርዳታ የሚሰጠውን የልጆች ፋፋ ቤተሰቡን በሙሉ ለመመገብ ማዋልና፣ ከቤት ውጭ በዋሉበት መመገብን ያካትታሉ።

ሌላው የምግብ እጥረትን የመቋቋሚያ ዘዴ በተለያዩ አነስተኛ ገቢ በሚያስገኙ እንቅስቃሴዎች መሰማራት ነው። ይህ የጉሊት ስራ፣ የወረቀት ሽያጭ፣ የልብስ እጥበት፣ እንጀራ መጋገር ፣ አረቄ ሽያጭ፣ የቀን ስራ፣ ቤት ማከራየት፣ ልመናና ሌሎች የቅጥርና የሙያ ስራዎችን ያጠቃልላል። ብዙ ቤተሰቦች ውስጥ ልጆችን ጨምሮ ሁለትና ሶስት ሰዎች በገቢ ማስገኛ ስራ ይሳተፋሉ። ከእነዚህ የገቢ ምንጮች ውጪ ጥቂት ቤተሰቦች የቤት ዕቃና የሴቶች ጌጣጌጦችን ለመሸጥ ሲገደዱ ብዙዎቹ የጥናቱ ተሳታፊዎች ግን ሊሸጥ የሚችል ንብረት እንደሌላቸው ተናግረዋል።

የአካባቢ ማህበራዊ ግንኙነቶችና ተቋሞች የምግብ እጥረት የመቋቋሚያ ዘዴዎች ምንጭ ሊሆኑ ይችላሉ። አንዳንድ ቤተሰቦች ከዘመዶቻቸው ወይም ከወዳጆቻቸው ገንዘብ መበደር ሲችሉ ብዙዎች ግን ይህንን ለማድረግ ሳይችሉ ወይም ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተዋል። የተወሰኑ ለከፍተኛ ችግር የተጋለጡ ቤተሰቦች ደግሞ በአካባቢ እድሮች በእቁብ ማህበራትና በጎረቤቶቻቸው በተለይ በበአላት ወቅት የገንዘብ ወይም የምግብ እርዳታ ይደረግላቸዋል። በዋጋ ንረት ምክንያት ማህበረሰቡ በገጠመው ችግር ምክንያት ግን ይህን ዓይነት የመደጋገፍ ልማዶች እየተዳከሙ መጥተዋል።

በድህነት ኑሮ ውስጥ የሚገኙ ቤተሰቦች የምግብ እጥረትን ለመቋቋም በሚጠቀሙባቸው ስልቶች ላይ አንዳንድ ማነቆዎች ይከሰታሉ። ከእነዚህም ውስጥ እንደ በሽታ፣ የአቅም ማነስና የእድሜ ብዛት የመሳሰሉት ሰዎች በገቢ ማስገኛ እንቅስቃሴዎች እንዳይሳተፉ ይከለክላሉ። ከገበያው ጋር የተያያዙ ማነቆዎችም የገቢ ማስገኛ እንቅስቃሴዎችን ሲያዳክሙ ይታያሉ። ከእነዚህ ውስጥ ለምሳሌ ሊገበያዩ የሚችሉ እንደ አረቄ መወደድ፣ ባለው የኀብረተሰብ የገንዘብ አቅም መዳከም ምክንያት ለጉልበት ስራ ያለው ፍላጎት መቀነስ፣ በገቢ ማስገኛ እንቅስቃሴዎች በሚሳተፉ ሰዎች መካከል ያለው ከፍተኛ ውድድርና፤ የእነዚህ እንቅስቃሴዎች ዝቅተኛ ትርፋማነት ይገኙበታል። የካፒታል እጥረትም ቤተሰቦች በአንዳንድ የገቢ ማስገኛ እንቅስቃሴዎች ያላቸውን ተሳትፎ በተደጋጋሚ ሲገድብ ይታያል። በእነዚህ እንቅስቃሴዎች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ከሚያሳርፉ የፖሊሲና አስተዳደራዊ እርምጃዎች ውስጥ በጥቃቅን የመንገድ ዳር ንግድ በሚያካሄዱ ሰዎች ላይ የሚደርሰው ወከባና በቤታቸው ወይም በሌላ ስፍራ አነስተኛ ንግድ የሚያካሄዱ ግለሰቦች እንዲከፍሉ የሚጠየቁት የኪራይ ክፍያ ይጠቀሳሉ።

## ከምግብ ዋስትና ጋር ተያያዥነት ስላላቸው የመንግስት ፖሊሲዎችና እንቅስቃሴዎች የነዋሪዎች አመለካከት

የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የታለሙ የመንግስት ፖሊሲዎችንና እንቅስቃሴዎችን በሚመለከት የጥናቱ ተሳታፊዎች የተለያዩ አስተያየቶችን ሰንዝረዋል። ከ2001 ዓ.ም ጀምሮ በመንግስት ድጎማ ለከተማ ነዋሪዎች የሚሸጠው ስንዴ የምግብ እጥረትን በመቅረፍ ረገድ አዎንታዊ ሚና እንዳለው ገልጸዋል። ነገር ግን በነፍስ ወከፍ እንዲሸምቱ የሚገደዱት የመቶ ኪሎ ግራም ኮታ ለብዙዎች ከፍላጎታቸውና ከአቅማቸው በላይ እየሆነ እንደሚቸገሩና የስንዴው አቅርቦት በየወሩ ቀጣይነት እንደሌለውም ገልፀዋል።

መንግስት እህልና ሌሎች ምግብ ነክ ቁሳቁሶችን በተመጣጣኝ ዋጋ ለማቅረብ የሚጠቀምበት ስልት የሸማቾች ማህበራትን በማደራጀት ነው። የጥናቱ ተሳታፊዎች ግን በአመዛኙ ማህበራቱ የታለመላቸውን ግብ መተዋል ብለው አያምኑም፣ ምክንያቱም የሽያጭ ዋጋቸው ገበያ ላይ ካለው ዋጋ እምብዛም ስለማይለይ ነው። ለዚህ እንደ ምክንያት የተጠቀሰው ማህበራቱ በቂ አቅም የሌላቸው መሆኑ ነው። በአንጻሩ መንግስት የእህልን የገበያ ዋጋ ለመቆጣጠር የሚያደርገውን ጥረት ብዙዎች ጠቃሚ ሆኖ ቢያገኙትም ሙሉ በሙሉ ውጤታማ ሆኗል ብለው አያምኑም።

ለገቢ ማስገኛ እንቅስቃሴዎች በተለያዩ ተቋማት የሚሰጥ ብድርም የተወሰነውን የሕብረተሰብ ክፍል እየጠቀመ ይገኛል። ሆኖም እንደ የስራ ቦታ እጦት፣ ብድር ለማግኘት እንደ ቅድመ ሁኔታ የሚጠየቁት የተያዥና የነዋሪነት፣ የትምህርትና የስራ ልምድ ማረጋገጫዎችና ብድሩን መልሰው መክፈል ባይችሉ በኃላፊነት የመጠየቅ ፍራቻ የህብረተሰቡን ተሳትፎ እየቀነሰ እንደሆነ ተገልጾአል።

ከላይ የተጠቀሱት የመንግስት እንቅስቃሴዎች በጎ ዓላማ ኖሯቸው በአፈጻጸማቸው ሊጠናከሩ እንደሚገባቸው ሲጠቆሙ በአመዛኙ አሉታዊ ሚና አላቸው ተብለው የሚታሰቡም ነበሩ። ከእነዚህም ውስጥ የነጻ ገበያው ስርዓት የምግብ ዋጋ ግሽበትና የምግብ እጥረት መንስኤ እንደሆነ በሰፊው ተቀባይነት ያለው አስተያየት ተንጸባርቋል። በተጨማሪም የመንገድ ዳር ንግድና ሌሎች የገቢ ማስገኛ እንቅስቃሴዎችን የሚያካሄዱ ሴቶች በደንብ አስከባሪዎች የሚደርስባቸው ወከባና በልማት ሥራ ምክንያት ለተፈናቀሉ በገቢ ማስገኛ እንቅስቃሴዎች የተሰማሩ ግለሰቦችም ሆነ የህብረት ስራ ማህበራት ተገቢውን ድጋፍ አለመስጠቱ በተወሰነው የህብረተሰብ ክፍል ዘንድ የምግብ እጥረትን እንዳባባሰ ተገልጿል።

### ከጥናቱ የመነጨ የከተማ ምግብ ዋስትና የፖሊሲና የፕሮግራም አቅጣጫዎች

በአዲስ አበባ በዝቅተኛ ገቢ የሚተዳደረው ሕብረተሰብ ለአስከፊ የምግብ እጥረት እንደተጋለጠ ጥናቱ ይጠቁማል። ይህንን ሁኔታ ለመቅረፍ የሚከተሉት የፖሊሲና የፕሮግራም አቅጣጫዎች ተጠቁመዋል።

## 1. የከተማ ምግብ ዋስትና ስትራቴጂ

የአገሪቱ የምግብ ዋስትና ስትራቴጂዎች ትኩረታቸው በገጠሩ ሕብረተሰብ ላይ ሆኖ ቢቆይም ጥናቱ የከተማው ሕዝብ የምግብ ዋስትና ከገጠሩ እምብዛም እንደማይሻል ጠቁሟል። ስለዚህም በሚቀጥለው የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ

የከተማውን የምግብ ዋስትና ጉዳይ ማካተት ያስፈልጋል፡፡ ይህ በመጀመሪያ ደረጃ የሚያመላክተው በገጠሩ እየተተገበረ ያለው የሴፍቲ ኔት ስትራቴጂ በከተሞች ለምግብ እጥረት ተጋላጭ የሆነውንም የሕብረተሰብ ክፍል ማቀፍ እንዳለበት ነው፡፡ ይህ የሴፍቲ ኔት ፕሮግራም በዝቅተኛ ገቢ የሚተዳደረውን ሕብረተሰብ በዕዳት፣ በመሠረተ ልማት ማሻሻያና በማህበራዊ አገልግሎት በማሳተፍ የገንዘብ ወይም የምግብ ድጎማ ማድረግንና በጉልበት ስራ መሳተፍ ለማይችሉ እንደ አዛውንት ከኤች አይ ቪ ጋር ለሚኖሩ ሰዎች እና ለወላጅ አልባና ለአደጋ ተጋላጭ ሕጻናት ቀጥተኛ እርዳታ ማድረግንም ያካትታል፡፡

## 2. በመንግስት የሚደጎም የስንዴ ሽያጭና የሸማቾች ማህበራት

በመንግስት ድጎማ ስንዴ ከውጭ እየመጣ ለሕዝብ የሚሸጥበት ፕሮግራም የከተማ ነዋሪዎች በተመጣጠነ ዋጋ እህል እንዲያገኙ የማድረግ ብቃቱን በማጠናከር ረገድ የሚወሰዱ እርምጃዎች የላቀ ፋይዳ ሊኖራቸው ይችላል፡፡ ከእነዚህ እርምጃዎች አንዱ የስንዴ ሽያጩን ፕሮግራም አፈጻጸም ማሻሻል ሲሆን ለምሳሌ የስንዴ ክፍፍሉ በየወሩ ሳይቋረጥ እንዲካሄድ ማድረግና ገዢዎች የፈለጉትን የእህል መጠን እንዲገዙ መፍቀድ ይቻላል፡፡ የስንዴ ሽያጭ ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ብቻ እንዲወሰን ማድረጉ ሊደገፉ የሚገባቸውን ቤተሰቦች በበለጠ ሊጠቅም ይችላል፡፡ የስንዴ ሽያጩን አፈጻጸም ከማሻሻል ውጪ በዓይነቱ የተለየና በገበያ ላይ የተመሰረተ ስርጭት መጠቀም የእህል ዋጋ በማረጋጋትና ከመጠንና ከዓይነት አኳያ የተጠቃሚዎችን ፍላጎቶች በማርካት ረገድ የተሻለ ውጤታማነት ሊኖረው ስለሚችል እንደ አማራጭ ሊታይ ይችላል፡፡

የሸማቾች ማህበራት እህል በተመጣጠነ ዋጋ ለማቅረብ የሚያስችላቸውን የገንዘብ አቅም የገበያ ትስስርና የማከማቻ ስፍራ ስለሚያንሳቸው እነዚህን በሚሟላት ረገድ ድጋፍ ይሻሉ፡፡

## 3. የስራ እድል ማስፋፋት

የስራ እድልን ለማስፋፋት የሚደረጉ ጥረቶች የምግብ ዋስትና በማጠናከር ረገድ ከፍተኛ ሚና እንደሚኖራቸው ጥርጥር የለውም፡፡ የዚህ ዓይነቱ ጥረት አካል መሆን የሚገባው የአነስተኛና የጥቃቅን የንግድ ድርጅቶችን የገንዘብና የቦታ ፍላጎት በሚሟላት የማጠናከር ስራ ነው፡፡ በተጨማሪም ለስራ አጥ ወጣቶችና ጎልማሶች የሚሆን በተናጠል የሚሰጥ የሙያ ስልጠናና የብድርና ክቀጣሪዎች ጋር የማገናኘት አገልግሎት ማስፋፋቱ አስፈላጊ ነው፡፡ በተጨማሪም ለስራ እድል መስፋፋት ድጋፍ ሊያደርግ የሚችል የፖሊሲና የአፈጻጸም ስርዓት በማመቻቸት ለምሳሌ በአነስተኛ ገቢ ማስገኛ እንቅስቃሴዎች ላይ የሚጣሉ የግብርና የኪራይ ክፍያዎችን መቀነስና በልማት ስራዎች ምክንያት ለተፈናቀሉ ድርጅቶችና በመንገድ ዳር የንግድ ስራ ላይ ለተሰማሩ ግለሰቦች አመቺ የስራ ቦታ መስጠት ተገቢ ነው፡፡

## 4. ለትላልቅ እርሻዎችና ለከተማ የምግብ ምርትና ዝግጅት ድጋፍ መስጠት

የከተማዎችንና የአገሪቷን የምግብ ዋስትና ዘላቂ በሆነ ሁኔታ ለማረጋገጥ የግል ትላልቅ እርሻዎችን በቆላማ የአገሪቷ ክፍሎች እንዲስፋፉ ድጋፍ መስጠት ያስፈልጋል፡፡ በከተሞች ክልል የሚመረት ምግብ ለነዋሪዎቻቸው የምግብ ዋስትና አይነተኛ አስተዋጽኦ ማድረግ ስለሚችል አመቺ ለሆኑ ሰብሎችና አታክልት ምርትና የበግ ዕርባታን ለመሳሰሉ እንቅስቃሴዎች ድጋፍ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ ለምሳሌ በከተማዎች ለኢንቬስተሮች ተሰጥተውም ሆነ ሳይሰጡ ጥቅም ላይ ሳይውሉ የሚቆዩ መሬቶችን በጊዜያዊ መልክ ለምግብ አምራቾች ለመስጠት የፖሊሲ፣ የህግና የአፈጻጸም ቅድመ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ይቻላል፡፡ ጠቃሚና ተመጣጣኝ ዋጋ ያላቸውን የምግብ ውጤቶች ዝግጅት በማስፋፋት የከተማ ነዋሪዎችን የምግብ ፍላጎት በይበልጥ ማሟላት ይቻላል፡፡

## 5. የልጆች አመጋገብ ሥርዓትን ማሻሻል

በቅርቡ በተጀመረው የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ለተሻለ የልጆች አመጋገብ ስርአትና ለቤተሰብ ምጣኔ ተገቢውን ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል፡፡ በትምህርት ቤት ውስጥ ተማሪዎችን የመመገብ ፕሮግራም ማስጀመሩ የአካል ብቃታቸውን ብቻ ሳይሆን የትምህርት ተሳትፏቸውንና ውጤታማነታቸውንም ስለሚያጠናክር በውል ሊታሰብበት ይገባል፡፡

**ያሬድ አማረ (ዶ/ር)**


**ምንጭ፡-** Yared Amare. *Urban Food Insecurity and Coping Mechanisms: A Case Study of Lideta Sub-city in Addis Ababa*. FSS Research Report No. 5. Addis Ababa: Forum for Social Studies (FSS), 2010.



ምስጋናና ማሳሰቢያ

ይህ ሰነድ የታተመው በለጋሾች ቡድን የገንዘብ ድጋፍ ነው፡፡ ለሰነዱ ይዘት ሙሉ ኃላፊነቱ የደራሲው ሲሆን በምንም ሁኔታ የለጋሾች ቡድንን ወይም የአሳታሚውን አቋም እንደሚያንፀባርቅ ተደርጎ መወሰድ የለበትም፡፡



**አድራሻ፡-** ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ፣ ፖ.ሳ.ቁ 25864 ኮድ 1000 ❄ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

**ስልክ** 011-629 78 88/91 ❄ **ፋክስ** 011-629 78 89

**ኢሜይል:** fss@ethionet.et ❄ **ድረ-ገፅ** www.fssethiopia.org.et